እንደ ዕውነቱ ከሆነ አገራችን ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ የካፒታል አበዳሪ ነበረች ለማለት ይቻላል:: ኢትዮጵያ ወደኋላ የቀረችው ካፒታል ስላጠራት ሳይሆን ጠብታ+ /ካፒታሏ/ በሚገባ በሥራ ላይ ባለመዋሉ ነበር::

አሁንም ትክክለኛ የፖለቲካ አስተዳደር ካገኘች አገራችን በራሷ ካፒታል በራሷ የተፈጥሮ ሀብት ልትለማና ልትራመድ ትችላለች:: እንበዓሉ ገና ያልገባቸው የኢኮኖሚ ዕድገት ዋና ዓላማው ለጥቂት ከበርቴዎች ትርፍ ማዳበር ሳይሆን የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል መሆን እንደሚገባው ነው:: በኢትዮጵያም ዕውነተኛ የሕዝባዊ መንግሥት ከተቋቋመ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ቅርንጫፎች በመንግሥት እጅ ተይዘው ኢንዱስትሪዎች በትርፍ ሳይሆን ለሰፊው ሕዝብ በሚሠጡት ሥራ ጠቃሚ ውጤትና አገልግሎት እየተመዘኑ በመቋቋማቸው አንዱ ሌላውን በመደገፍና ሰፊ ገበያ ባገሩ ውስጥ በመፍጠር የአገሪቱን የኢኮኖሚ እርምጃ ለማፋጠን ይቻላል::

በቅርቡ የደረሰው የዓለም ታሪክ እንደሚያሳየው ከፍተኛ የኢኮኖሚና የሕብረተሰብ ለውጥ ያደረጉት አገሮች በራቸውን ለውጭ ከበርቴዎች ከፍተው የተበዘበዙት ሳይሆኑ እነዚህን የሕዝብ ጠላቶች አንቅረው ተፍተው ነፃ የሆነ ኢኮኖሚ የገነቡት ናቸው:: ለዚህም የሕዝባዊት ቻይና ታምራዊ እርምጃ ኗሪ መስክር ነው:: የውጭ ከበርቴዎች ድቀት እንጂ ልማት አያስገኙም::

ለነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚ እንታገል
ኢምፔሪያሊስቶችና ቡችላዎቻቸው ይጥፉ: